ኑ! ፊልሙ አሁን ይጀምራል፡፡

## በእንስሳት አለም ውስጥ ያለ የእናት ፍቅር እና እገዛ

እናንተ ትናንሽ ደስ የምትሉ ህፃናት ነበራችሁ፡፡

ወላጆቻችሁ በሚገባ ተንከባክበው እና ከማንኛውም አደጋ ጠብቀው አሳደጓችሁ፡፡

የምትመለከቷቸው ደስ የሚሉ እንስሳት ገና ህፃናት ናቸው…

ትንሽ እና ደካማ ስለሆኑ መመገብ እና መጠበቅ ይኖርባቸዋል፡፡

ወላጆቻቸው ከአደጋ ይጠብቋቸዋል፣ይመግቧቸዋል እንዲሁም ትልቅ መስዋእትነትን ይከፍሉላቸዋል፡፡

ኑ! እንስሳቶች ለልጆቻቸው የሚደርጉትን መስዋዕትነት እና እርስ በርስ ያላቸውን ትብብር በጋር እንመልከት፡፡

### አእዋፍ

*ገፀባህሪይ፡ እንዴት ናችሁ ልጆች! እኛ ወፎች ጫጩቶቻችንን ስለምንወድ በደንብ እንንከባከባቸዋለን ልክ እንደ ሌሎች ጓደኞቻችን በቅድሚያ የምናስበው ለልጆቻችን ነው፡፡ ኑ! አሁን አንዳንድ ጓደኞቻችን ለልጆቻቸው ምን እንደሚሰሩ እንመልከት፡፡*

እነዚህ አሁን የተፈለፈሉት ጫጩቶች መብረር ስለማይችሉ የራሳቸውን ምግብ ማግኘት አይችሉም፡፡

ሲራቡ አፋቸውን በመክፈት እናታቸው እና አባታቸው ምግብ እስኪያመጡላቸው ይጠብቃሉ፡፡

የነዚህ ወፎች እናት እና አባት ቀን ተሌት ለእነሱ ምግብ በመሰብሰብ በጥንቃቄ ይመግቧቸዋል፡፡

ተመልከቱ! ይህ የባህር ውስጥ ሰጣሚ ወፍ ለጫጩቶቹ ምግብ በመሰብሰብ የተራቡ ህፃናት ወደሚገኙበት ከወንዙ በስተጀርባ ወዳለው ጎጆው ይሄዳል፡

እነዚህ ወፎች ለልጆቻቸው ምግብን ያለድካም በየአስር ደቂቃው ያመላልሳሉ፡፡

ከእራሳቸው በፊት ስለ ጫጩቶቻቸው ነው የሚያስቡት፡፡

ሆኖም ልጆች ወፎች ብቻ አይደሉም ስለልጆቻቸው የሚያስቡት…

ብዙ እንስሳቶች ከወፎች የበለጠ መስዋእትነት ለልጆቻቸው ይከፍላሉ፡፡

አላህ  ነው አነዚህ እንስሳት ለልጆቻቸው እንዲያስቡ እና እንዲመግቧቸው ያደረጋቸው፡፡

አላህ (ሱ.ወ) የስሜት ህዋሳቶቻችንን እንደሰጠን ሁሉ ለእንስሳቶም እንዲኖሩ እና እንዲራቡ ተፈጥሮአዊ ስጦታዎችን ሰጥቷቸዋል፡፡
ለሰው ልጆች መመሪያ ይሆን ዘንድ አላህ (ሱ.ወ) ባወረደው ቁርአን ላይ አላህ (ሱ.ወ) እንስሳት ለመኖር ከሚያስፈልጋቸው ችሎታዎች ጋር እንደተፈጠሩ ገልጿል፡፡

**"ምድር ላይ ያሉም÷ በሁለት ክንፎቻቸው የሚበሩትም በራሪ እንስሳት በየፊናቸው እንደ እናንተው በጋራ የሚኖሩ ፍጡራን ናቸው፡፡ ከመፅሀፍ ውስጥ ሳናሰፍር የተውነው ምንም ነገር የለም፡፡ ከዚያም ሁሉም ወደ ጌታቸው ይሰበሰባሉ፡፡" (ሱረቱል አንአም፡38)**

## ስቶርኮች

ኑ! ልጆች ወደ ታይላንድ ደን እንጓዝ፡፡
እዚህ በጣም ይሞቃል፡፡
እንዴት ነው እዚህ የተወለዱ ትናንሽ ስቶርኮች ከሙቀቱ እራሳቸውን ሚጠብቁት?
የሚኖሩት ወላጆቻቸው በምንቃራቸው በሚያመጡላቸው ውሀ ነው፡፡
ወደ አባት እና እናት ስቶርኮች ተመልከቱ! ገና ላባ ባላወጡት ልጆቻቸው ላይ ውሃ እየጨመሩላቸው ይገኛሉ፡፡
ይህ ቀዝቃዛ ሻወር ጫጩቶችን ለጥቂት ጊዜ ፋታ ይሰጣቸዋል፡፡ ነገር ግን ይህ ብቻ በቂ አይደለም፡፡
ጫጩቶቹ ጥላም ያስፈልጋቸዋል፡፡
ይህ ፍላጎትም በወላጆቻቸው መስዋእትነት ይሞላል፡፡
ግን እንዴት ክንፎቻቸውን በመክፈት ከሞቃቷ ፀሀይ እንደጥላ በመሆን ጫጩቶችን ከሙቀት ሊጠብቁ ቻሉ?
ስቶርኮች ለልጆቻቸው በሚያሳዩት እንክብካቤ፣ ባላቸው ትስስር እና ራስን መስዋዕት በማድረግ ከአለማችን አርአያ  ወላጆች አንዱ ናቸው፡፡

## ዳክዬዎች

ብዙ ዳክዬዎች ጫጩቶቻቸውን በላባዎቻቸው መሀል ይሸከሟቸዋል፡፡
እናትዬው ወንዝ ዳርቻ ስትደርስ የልጆቿ የመውጫ ጊዜ ነው፡፡
እናትዬው ልጆቿ ይመቻቸው ዘንድ ጎጆውን ታስተካክለዋለች፡፡

በዚህ ጊዜ አባትዬው ለእነሱ ምግብን ይፈልጋል፡፡

አባት ዳክዬ ወደ ጎጆው በመመለስ ጫጩቶቹን በጥንቃቄ ይመግባል፡፡

ከተመገቡ በኋላ ደህንነቱ ወደተጠበቀው ቦታ በድጋሚ ይመለሳሉ፡፡

ይህ ደህንነቱ የተጠበቀ ቦታ የእናታቸው ክንፍ ነው፡፡

## ዶልፊኖች

በእናት እና በልጅ ዶልፊን መካከል የጠበቀ ግንኙነት አለ፡፡

እናትዬው ልጇን ስለእያንዳንዱ አደጋ ታስተምረዋለች፡፡

አደጋው ይህ ነው!

ትናንሽ ዶልፊኖች ከጀልባ ጋር እየተወዳደሩ ነው፡፡

ከዶልፊኖቹ አንዱ ወደ ጀልባው በጣም መጠጋቱን አላወቀም፡፡ የጀልባው ውልብልቢት ወይም አካሉ ሊጎዳው ይችላል፡፡

እናትዬው ዶልፊን አደጋውን በማየት ወደ ልጇ ጎን በመሄድ ልጇን ወደታች ትገፋዋለች፡፡

ክፍተኛ የድምፅ ሞገድ ከአፍንጫዋ በማመንጨት ወደ ህፃኑ ላከች፡፡

በነዚህም ሞገዶች ለልጇ ማስጠንቀቂያ ትሰጣለች፡፡

ህፃኑ ጥፋቱን ይረዳል፡፡

ከዚያም ሁለቱም አብረው ይዋኛሉ፡፡

# ዝሆኖች

*ገፀባህሪ፡በእንስሳት አለም ውስጥ ያሉ የፍቅር እና የአንድነት ምሳሌዎችን ማየት ትፈልጋላችሁ?*

ዝሆኖች የየብስ ትላልቅ እንስሳት ሲሆኑ ሊጠቀስ የሚገባው ባህሪያቸው የእርስ በርስ ግንኙነታቸው ነው፡፡

የራስ መስወእትነት እና መረዳዳት በቤተሰብ አባላት ብቻ የተወሰነ ሳይሆን በመላው መንጋ ላይ የሚታይ ባህርይ ነው፡፡

ሞቃታማ የበጋ ቀን በአፍሪካ ሜዳ ላይ…

ዝሆኖች ምግብ እና ውሀ ለማግኘት በመንዝ ላይ ይገኛሉ፡፡ ይህ መድረቅ የጀመረ ሀይቅ በአከባቢው ብቸኛ የውሀ ምንጭ ነው…

ለዚህ ኩንቢው አጭር ለሆነ ትንሽ ዝሆን ውሀውን መድረስ አስቸጋሪ ሆኖበታል፡፡ ውሃውን ለመድረስ መንበርከክ ይኖበታል፡፡

ትልቁ ዝሆን ህፃኑን በድንገት በመምታት ውሀ ውስጥ ከተተው፡፡

ህፃኑ አሁኑኑ ካልደነ ጭቃ ውስጥ ሰጥሞ ሊሞት ይችላል…

ህይወቱን የማትረፊያ ጊዜው አጭር ነው…

እናትዬው ዝሆን በመንበርከክ ኩንቢዋን ከህፃኑ ስር በማድርግ ጎትታ ልታወጣው ትሞክራለች፡፡

ሌሎች ዝሆኖች ወደዚህ ቦታ መጥተው ልጁን ከጉድጓድ ለመጎተት በመሞከር እናትዬዋን ያግዟታል፡፡

ተጎጂውን የማዳኑ ስራ በዚህ መልኩ ይጀምራል፡፡

ጉድጓዱ በመጠኑ ሩቅ ነው፡፡ ስለዚህ አንዳንድ ዝሆኖች በጉድጓዱ ዙሪያ በመቆፈር ህፃኑን በቀላሉ ለመድረስ ይሞክራሉ፡፡

በመጨራሻ ትንሹ ዝሆን ድኗል፡፡ ሁሉም በመንጋው ውስጥ ያለ ዝሆን ወደ ህፃኑ በመምጣት በኩንቢው ያሻሽዋል፡፡

በመንጋው አባላት መካከል ያለው ትስስር እና መረዳዳት የህፃኑን ህይወት አዳነ፡፡

ይህ በእንስሳት አለም ውስጥ ያለ አስደናቂ የራስ መስዋዕትነት የአላህ ፈጣሪነት አንዱ ተአምር ነው፡፡ በአንድ የቁርአን አንቀጽ አላህ እንዲህ ይላል፡፡

**"እናንተን መፍጠሩም÷ ምድር ላይ እንስሳትን መርጨቱም ፅኑ እምነት ላላቸው ሰዎች ተአምራት ናቸው፡፡" ሱረቱል ጃሲያ፡4**

## የአረብ ወፎች

ይህ መካከለኛው ምስራቅ ነው…

በዚህ ሞቃታማ እና ደረቅ አካባቢ መኖር በጣም አስቸጋሪ ነው፡፡

ይህ የአረብ ወፍ በመባል የሚታወቀው ትንሽ ወፍ በዚህ አስቸጋሪ ቦታ ላይ መኖር ይችላል፡፡

ይህም ሊሆን የቻለው በነዚህ ወፎች መካከል አስደናቂ ህብረት እና አንድነት ስለሚገኝ ነው፡፡ ሁሉንም ነገር በጋራ ያከናውናሉ፡፡

ገላቸውን ከታጠቡ በኋላ እራሳቸውን በፀሀይ ያደርቃሉ፡፡

ክንፎቻቸውን በሚደርቁበት ጊዜ አንዱ ወፍ የሌላኛውን ወፍ አካል ያፀዳል፡፡

ይህ ለጤናቸው እጅግ ጠቃሚ ነው፡፡

ሳይታክቱ  እና ሳይሰለቹ እርስ በርስ ይበጣጠራሉ፡፡

በአረብ ወፎች መካከል የስራ ክፍፍልም ይገኛል፡፡ ለምሳሌ ሁሉም የመንጋው አባል ለጫጩቶቹ ምግብን ይፈልጋል፡፡ በኋላ ላይም የተሰበሰበውን ምግብ አኩል ይካፈሉታል፡፡

መንጋውን የመጠበቅ ኃላፊነትም በተራ ይሰራል፡፡

ሁሉም ወፍ ተራው ሲደርስ ዛፍ ላይ በመውጣት መንጋውን ይጠብቃል፡፡ ጠባቂው ወፍ የመቀየሪያ ሰዓቱ ሲደርስ ተረኛው ጠባቂ ትንሽ ምግብ ለጠባቂው በማምጣት የተራውን መጠበቅ ይጀምራል፡፡

ይህ ጥበቃ ለመንጋው ደህንነት እጅግ ጠቃሚ ነው፡፡

በመጠበቅ ላይ የሚገኘው የአረብ ወፍ አደጋ ሲመጣ የማስጠንቀቂያ ድምጽ አሰማ፡፡

ሁሉም መንጋ እራሱን ለመጠበቅ ተሰበሰበ፡፡ ጠላታቸው እንዲረበሽ በማድረግ ሀሳቡን ይሰርቁታል፡፡

አደጋው ከቦታው ሲርቅ ህይወት ወደቀድሞው ገፅታዋ ትመለሰለች፡፡

ጠባቂውም ወደ ቦታው ይመለሳል፡፡

ጫጩቶቹ አብረው መጫወት ጀመሩ፡፡

ደህና!እንዴት ነው እነዚህ ወፎች እንዲህ አይነት ጠንካራ ህብረትን ሊያሳዩ የቻሉት? የምትመለከቷቸው ወፎች ህሊና የሌላቸው እንስሳት ናቸው፡፡

እነዚህ በረው ምግብ በመፈለግ የራሳቸውን ሆድ ይሞላሉ ተብለው የሚገመቱ እንስሳት ለምን ጓደኞቻቸውን ይጠብቃሉ?

ከዚህ ግምት በተቃራኒው ከፍተኛ መስዋእትነት ይከፍላሉ፡፡

ምንም ሳይመገቡ በቆራጥነት የጥበቃ ስራውን ያካሂዳሉ፡፡

ማነው ለነዚህ ወፎች የራስ መስዋእትነትን ያስተማራቸው?

ለመሰሎቻቸው ሲሉ እራሳቸውን አደጋ ላይ እንዲጥሉ ያዘዛቸው ማነው?

በርግጥም እነዚህን ትናንሽ ወፎች ከምንም ያስገኘው ሀያሉ አላህ ነው ትብብራቸውን፣ አንድነታቸውን እና የራስ መስዋእትነታቸውን ያለገሳቸው፡፡

## ኒልካቶች

እነዚህ ኒልካት በመባል የሚታወቁ ትናንሽ እንስሳት በጋራ ይኖራሉ፡፡

በመካከላቸው አስደናቂ አንድነት ይስተዋላል፡፡

በአደገኛ አካባቢ ስለሚኖሩ አንድነት እጅግ ያስፈልጋቸዋል፡፡

ሁልጊዜ ጠዋት ኒልካቶች የደህንነት ፍተሻቸውን ካካሄዱ በኋላ ምግብ ለመፈለግ በአካባቢያቸው ላይ ይሰራጫሉ፡፡

በዚህ ማህበራዊ ኑሮ ላይ እያንዳንዱ አባል የራሱ የሆነ ሀላፊነት አለው፡፡

ጥቂት ኒልካቶች ለሌሎች ደህንነት ጥበቃ ያደርጋሉ፡፡

ይህ የምትመለከቱት ኒልካት ከጀርባ ሊመጣ የሚችለውን አደጋ በመጠበቅ ላይ ይገኛል፡፡
አንዳንዶች በዛፍ ጫፍ ላይ ጥበቃ በማድረግ እራሳቸውን መስዋእት ያደርጋሉ፡፡
ምንም ሳይበሉ እና ሳይጠጡ በጠራራ ፀሀይ ለሰዓታት ይጠብቃሉ፡፡
ጠባቂው ኒልካት አደጋ መምጣቱን ሲያይ ጓደኞቹን የማስጠንቀቂያ ድምፅ ያሰማቸዋል፡፡
ድምፁን ሲሰሙ ኒልካቶቹ ወደ ጉድጓዳቸው ለመደበቅ ይሮጣሉ፡፡
የእርስበርስ መተባበር እና ህብረት የኒልካቶቹን ህይወት አዳነ፡፡
የቡድኑ እጅግ ወሳኙ ሀላፊነት የኒልካቶችን ልጆች መንከባከብ እና ማሳደግ ነው፡፡
ሁልጊዜ አንድ ኒልካት ህፃናቱን ለመንከባከብ በጉድጓድ ውስጥ ይቆያል፡፡
ይህ በኒልካቶች መካከል የሚታየው አስደናቂ ህብረት፣አንድነት እና ራስን መስዋዕት የማድረግ ባህሪይ በአላህ (ሱ.ወ) የተቸራቸው ነው፡፡

## በቀቀኖች

እነዚህ የአውስትራሊያ የበቀቀን ጫጩቶች ናቸው፡፡
እነዚህ ጫጩቶች እያንዳንዳቸው በአምስት ቀን ልዩነት ነው የተወለዱት፡፡
ለዚያ ነው በመጠን የተለያዩት፡፡
መጀመሪያ የተፈለፈለው ጫጩት ከመጨረሻው ይበልጣል፡፡
ሆኖም እናት በቀቀን ፍትሀዊ ናት፡፡
ለእንዳንዱ ጫጩት የሚያስፈልገውን ምግብ ትሰጠዋለች፡፡
ከ አስር ቀናት በኂላ ትልቁ ጫጩት ከሌሎች እንደቀድሞው በደንብ ይበልጣል፡፡
ነገር ግን በሚያስገርም ሁኔታ ምግቡን ትንሽ እና ደካማ ከሆነው ወንድሙ ጋር በመካፈል በራሱ አፍ ይመግበዋል፡፡
ለምን ይህ ትንሽ ጫጩት ይህን የመሰለ የራስ መስዋእትነትን ያሳያል?
ለምን ለደካማ ወንድሙ ምግብ ይሰጠዋል?
እንስሳት ለራሳቸው ብቻ ነው የሚያስቡት ብለው የሚናገሩ ሰዎች ይህን በጎ ባህሪ በፍፁም ማብራራት አይችሉም፡፡
እንደተመለከታችሁት ትንሹ ወፍ እንኳን ምግቡን በአስፈላጊው ጊዜ ከትንሽ እና ደካማ ወንድሙ ጋር ይጋራል፡፡
አላህ በሰጣቸው አንድነት እና አብሮ የመካፈል ባህሪይ ሁሉም ልጆች በጤናማ ሁኔታ ያድጋሉ፡፡

## ግንደ ቆርቁር

የግንደ ቆርቅር መንቆር እጅግ ጠንካራ መቦርቦሪያ ነው፡፡ መጀመሪያ ዛፍ ላይ በመንቆሩ ጓድጓድ ይሰራል፡፡ በመቀጠል በክረምት ለምግብነት በሚጠቀምባቸው የበሉጥ ዛፍ ፍሬዎች ይሞላዋል፡፡ በዛፍ ላይ የምትመለከቷቸው ግንደ ቆርቁሮች ስልሳ ሺህ የበሉጥ ዛፍ ፍሬዎችን አከማችተዋል፡፡ በዛፍ ልጣጭ ላይ ስልሳ ሺህ ቀዳዳዎችን መስራት በጣም አስቸጋሪ ነው፡፡

ሆኖም ግንደ ቆርቁሮች ይህን ከባድ ስራ በትዕግስት እና በመስዋዕትነት ይወጡታል፡፡

አላማቸው በቀዝቃዛዎቹ የክረምት ቀናት ቤተሰቦቻቸውን መመገብ ነው፡፡

ወጣት የቤተሰብ አባላት በዝግጅቱ ላይ ይሳተፋሉ፡፡

ሁሉም ወፎች ሀላፊነታቸውን በአግባቡ ይወጣሉ፡፡

የትኛውም ወፍ አሻፈረኝ አይልም፡፡

የግንደ ቆርቁር ቤተሰብ በሕብረት እና በአንድነት ተምሳሌትነታቸው ለመጪዎቹ አስቸጋሪ ጊዜያት ይዘጋጃሉ፡፡

## መደምደሚያ

እሺ! ልጆች በዚህ ፊልም ላይ እንስሳቶች ለልጆቻቸው የሚያደርጉትን እንክብካቤ እና በመካከላቸው ስላለው አንድነት ምሳሌዎችን አይተናል፡፡

አላህ (ሱ.ወ) እንስሶቶችን ፈጥሮ የመተሳሰብ፣ የእዝነት እና ራስን መስዋዕት የማድረግ ባህሪያትን ሰጥቷቸዋል፡፡

በቁርአን ላይ የአላህ እውቀት እና ሀይል ሁሉንም ነገር እንደሚያጠቃልል ተገልጿል::

**"አላህ ሰባት ሰማያትን የፈጠረ አምላክ ነው፡፡ ከምድርም መሰላቸውን ፈጥሯል፡፡ አላህ ሁሉንም ነገር አዋቂ መሆኑን ታውቁ ዘንድ ይህን ገልፆላችኋል፡፡"** (ሱረቱ ጠለቅ፡12)

## ይህን ያውቁ ኖሯል

**ሻምፒዮን ወፎች**

እንዴት ናችሁ ልጆች! አንዳንድ ወፎች መብረር አይችሉም፡፡ነገር ግን ሌሎች የተለያዩ ችሎታዎች አሏቸው፡፡

ለምሳሌ ሰጎን የኦሎምፒክ ሪከርድን ከሰበረ አትሌት በተሻለ ፍጥነት መኖጥ ትችላለች፡፡ የሰው ልጅ ከሰጎን ጋር የአንድ መቶ ሜትር የሩጫ ውድድር ቢያደርግ የሰውልጅ በሩጫው ተሸናፊ

ይሆን ነበር፡፡ የኦሎምፒክ ሻምፒዮን በሰዓት ሰላሳ ኪሎ ሜትርን ሲሮጥ በሰዓት ሰጎን ስልሳ ኪሎ ሚትሮችን መሮጥ ትችላለች፡፡ በረጅም እግሮቿ በአንድ እርምጃ ሶስት ሜትር መሄድ ትችላለች፡፡

እነዚህ የአእዋፍ ዝርያዎች በእንስሳት አለም ውስጥ ፈጣን ሯጮች ናቸው፡፡ ያላቸውን ችሎታ የሰጣቸው ሁሉንም ነገር ከምንም ያስገኘው ኃያሉ አላህ ነው፡፡

## የስቶርኮች ስደት

ስቶርኮች በየአመቱ ይሰደዳሉ፡፡

ከአፍሪካ አህጉር በመነሳት አውሮፓ ለመድረስ የሜዲትራንያን ባህርን ያቋርጣሉ፡፡

ጥሩ! ስቶርኮች በዚህ አንድ ሺህ ኪሎ ሜትርን በሚረዝም መንገድ እንዴት ሳይጠፉ የፈለጉበት ቦታ መድረስ ቻሉ?

ጥናቶች የመሬትን ማግኔታዊ ፊልድ የሚለይ ኮምፓስ በስቶርኮች አካል ውስጥ እንደሚገኝ አረጋግጠዋል፡፡

በዚህ ተፈጥሮአዊ ኮምፓስ የመሬትን ማግኔቲክ ፊልድ መስመሮችን በመከተል አቅጣጫቸውን ያስተካክላሉ፡፡

ለዚህ ኮምፓስ ምስጋና ይግባው ጉዞውን በማጠናቀቅ ከአመት በፊት ይኖሩበት የነበረውን ጎጆ ያገኙታል፡፡

ይህን አቅጣጫ የማግኘት ስርዓት በስቶርኮች አካል ውስጥ ያስቀመጠው ሁሉንም እንስሳቶች የፈጠረው ሀያሉ አላህ ነው፡፡